# <u>የግንቦት 23 (1990 ዓ.ም) ሰማዕታቶቻችንና በሻዓቢያ የታገቱ ዜጎቻችን አይረሱም!</u>

## <u>የኢሮብ ሙብት ተሟጋች ማሕበር (መ.ኢ.ተ.ማ)</u>

ሻዕቢያ የተራዘመ ጊዜ ወስዶ ወታደራዊ ዝግጅቱን ካደረገ በኋላ፤ ግንቦት 1990 ዓ.ም መካናዝድ ሠራዊት በማሰማራት ኢትዮጵያ ላይ በተለያዩ ግንባሮች ጦርነት መክፈቱ የሚታወስ ነው። ይህ በሻዕቢያ የተሰማራው ግፈኛ ወራሪ ሠራዊት በደረሰበት ሁሉ በሲቭል ህብረተሰብና በንብረቱ ላይ ያደረሰው ውድመት እጅግ ከባድ እንደነበረ በምሬት የምናስታውሰው ሃቅ ነው። ከዚህ ውጭ አንባቢ ልብ እንዲልልን የምንፈልገው የዚህ መግለጫ ዓላማ የሻዕቢያ ግፈኛ ወራሪ ሠራዊት በየግንባሮቹ ያደረሰውን ጥፋት ተዘርዝሮ የሚያልቅ እንዳልሆነ ኢ.መ.ተ.ማ በሚገባ የሚገነዘበው ቢሆንም በተጨበጠ መረጃ እጥረት ምክንያትና መ.ኢ.ተ.ማ ድምጹን የሚያሰማለት ያጣውን የኢሮብ ህዝብ ድምጽ ለመሆን ካለው ዓላማ አንፃር፤ መረጃው ባለን በሽመዛና ግንባር የገባው ወራሪ ሓይል በኢሮብ መሬት በሰውና በንብረት ላይ ያደረሰውን ውድመት ላይ ብቻ ትኩረት እንድናደርግ መገደዳችንን ነው ከዚህም ቢሆን መጀመርያ ወረራው በተጀመረ ጊዜ የመከላከል ውጊያውን በጅግንነት በተዋጉ አርበኞች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው ። ይህ ማለት ግን በሁሉም ግንባሮች እናት አገራቸውን ለመከላከል ለተዋደቁ ኢትዮጵያዊያን ያለን አክብሮት፤ አድናቆትና ወገናዊ ስሜት የሚቀንሰው አይደለም።

<u>የሽመዛና ግንባር</u>፤

ግንቦት 23 ቀን 1990 ዓ.ም ግፈኛው የሻዕቢያ ሠራዊት ለወረራ ወደዚህ ግንባር ሲላክ የተሰጠው ተልእኮ በአድጋዲ-ዓረና በዓይጋ በኩል ወረራውን በመጀመር እግረ-መንገዱን ሰውና ንብረት እያወደመ እስከ ዓሊተና ያለውን የኢሮብ መሬት ባጭር ጊዜ ውስጥ በቊጥጥር ሥር ማዋል ነበር። ግፈኛው ወራሪ ሠራዊትም በተቀመጠለት እቅድ መሠረት በጉዞው ያገኘውን የህዝብ ንብረት እያወደመና እየዘረፈ ህዝቡንም እያሰቃየ ጉዞውን ጀመረው። ሆኖም፤ ይህ ግፈኛ ሠራዊት ድንበሩን ተሻግሮ ወደ አድጋዲ-ዓረና የዓይጋ ከፍታዎች ሲያመራ የተመለከተው የኢሮብ ህዝብ ባህላዊ የመልእክት ማስተላለፍያ ዜዴውን ተጠቅሞ የወረራው ወሬ ባንዴ መላዋን ኢሮብ አዳረሰ። በዚህ መሠረትም ከ50 የማይበልጡ አንስተኛ ትጥቅ የታጠቁ የአካባቢውን ምልሻ በማስቀደም እነሱን አጅቦ ወራሪውን የሻዕቢያ ሠራዊት ለመመከት ቆፎው እንደተነካበት ንብ ባንዴ ከየአቅጣጫው ወደ ዓይጋ ኮረብቶች ተመመ። በነዚህ የዓይጋ ከፍታዎችም ለ3 ቀናት ከወራሪው የሻዕቢያ ሠራዊት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ እየተናነቀ ተዋደቀ። ዳር ድንበሩን ላለማስደፈርም የበርካታ ጀግኖች ልጆቹን ህይወት ገበረ። በተጠቀሰው ጊዜ በዓይጋ አከባቢና በአድጋዲ-ዓረ ውድ ህይወታቸውን ለዳር ድንበራቸው ከሰዉት መካከልም ለጊዜው ስማቸውን ያገኘናቸው የውድ አርበኞቻችን ዝርዝር የሚከተለው ነው።

1. ፍሱሕ መድኅን ጻዕዱ(ጋራሳ)
2. አብራሃ ገብራይ ሓጎስ (ዋርዓትለ)
3. ካሕሳይ ሃይሉ ዚግታ (ዋንካቦ)
4. ኃይሉ ሓጎስ ስብሓት (ዓይጋ)
5. ኪዳነ ተስፋይ ሓጎስ (ዓውዳ)
6. ብሥራት ካሕሳይ ፃዕሩ (ማካታ)
7. ምስግና ካሕሣይ ሓጎስ (ማካታ)
8. ዎልዱ ተስፋይ ስብሓት (ኣራዕ)
9. አብርሃ መድኅን (አራዕ)
10. ተስፋይ ግርማይ አውዓላ (ሓሓይት)
11. ወልደገርግስ አማረ ዲሊቢስ (ዳያ)
12. ዮሃንስ ወልዱ ተስፋይ (ዓይጋ))
13. ማርሶ ወልደጊዮርግስ (ሓውዘን)

በዓይጋ ኮረብታዎች ከተካሄደው የፀረ-ሻዓቢያ ጦርነት በሕይወት ተርፈው ከጥቂት ቀናት በኋላ በሻዓቢ ቃኝዎች ማጋዑማ ላይ የተሰዉ የኢሮብ አርበኞች ስም ዝርዝር፤

1. በርሀ ተስፋይ ፍሱሕ (ሳብዓታ)
2. ሓሳባላ አብርሃ ሓጎስ (ሞሲጋደ)
3. ገብረዮሃንስ ኪዳኑ ወልዱ (ሞሲጋደ)
4. ኢያሱ ሓጎስ ሃዉኩ (ዋርዓትለ)

ይህ የስም ዝርዝርና እያንዳንዳቸው የተወለዱበት ቦታ እንደሚያመላክተው በዛን ጊዜ የተሰዉት አርበኞቻችን ከሶስቱም የኢሮብ ክፍሎች (አድጋዲ-ዓረ፣ ቡክናይቲ-ዓረ፣ ሐሳባላ) የተውጣጡ ሲሆን፤ የኢሮብ ህዝብ ሲወረር ቁሜ ማየት አልሻም ብሎ በጅግንነት አብሯቸው የተሰዋው ማርሶ ወልደጊዮርጊስም በአርበኞች ሰፈር ውሏል።

በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ በመጀመርያ ቀናት የተሰዉ አርበኞች ስም ወይም በስሕተት የተካተቱ ስሞች ቢኖሩ፤ የአባታቸው፤ አያታቸው ወይም የተወለዱበት አከባቢ ስም በትክክል ያልተገለጹ ቢኖሩ ካለማወቅ እንጂ ላገራቸው ሲሉ ውድ ሕይወታቸውን ከሰጡት አርበኞቻችን መካከል አንዱን ከሌላው ለማስቀደም ታስቦ እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል። ከዚህም ሌላ፤ መ.ኢ.ተ.ማ ግንቦት 23 የአርበኞቻችን ቀን ሆኖ መዘከር እንዳለበት ያምናል። ወረራን ለመከላከል የመጀመርያው ጥይት የጮኸውም በዛን ዕለት ነበር። በዕለቱ የአርበኝነት ውጊያውን ከተዋጉና ካዋጉት አርበኞች መካከል ከላይ ስማቸው የሠፈረው አልበገር ባይ ጀግኖች ነበሩበት። በመሆኑም፤ በሁለት ዓመት ጦርነት ውስጥ የተሰዉትን አርበኞች ስሞች ሁሉም ለመዘርዘር ባለመቻሉ መ.ኢ.ተ.ማ የጀግኖች ዕለት ብሎ በሰየመው ቀን ወደር ኣልባ ጀግንነት ሠርተው ያለፉትን ጀግኖች ስም ብቻ በመጥቀስ ሊያልፈው መገደዱን ለማሳሰብ ይወዳል።

ይህ ግፈኛ ወራሪ የሻዓቢያ ሠራዊት ለወረራ ተግባሩ ማስፈጸምያ የሚያገለግለውን የከባድና ቀላል መሣርያዎች ትጥቅ በየዓይነቱ አሟልቶ እስካፍንጫው ታጥቆ የመጣ ሲሆን፤ ከ50 የማይበልጡት የኢሮብ የአከባቢ ምልሻ የታጠቁት ግን ቀላል መሳሪያዎችን ብቻ ነበር። ቢሆንም ከትጥቅ ብዛትና ዓይነት ይልቅ አገርወዳድነት፤ ልበሙሉነት፤ የሞራል የበላይነት፤ ጽናትና ቆራጥነት በጦርነት ውስጥ የበለጠ ዋጋ እንዳላቸው በግንቦት 23 በዓይጋ ከፍታዎች የሻዓቢያን ወራሪ ጦር ጋር የተፋለሙት "ዕጡቃት ሰንበት" (የሰንበት ታጣቂዎች) የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ኢሮቦች በሚገባ አስመስክሯል። እስከ አፍንጫው ታጥቆ የመጣውን የሻዓቢያ ሠራዊትን ለሶስት ቀናት ገትሮ መያዝ ብቻ ሳይሆን የኢሮብ ድንበር ለቆ እስከወጣ (እስከ ሰንዓፈ ድረስ) ለማሳደድም ችሎ ነበር። ሆኖም ግን ከኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ይህንን ህዝባዊ ኃይል ለመታደግ የሚችል ረዳት ሃይል ወይም መሳሪያ ስላልተላከ በዓይጋ ተራሮች ተሸንፎ የተባረረው የሻዕቢያ ሠራዊት እንደገና ተሰባስቦና በተጨማሪ ሃይል ራሱን አጠናክሮ ተመልሶ በመምጣት ሰፊ የኢሮብን መሬት ለመቆጣጠር ችሏል።
ይህ ወራሪ ሠራዊት በተቆጣጠራቸው ግዛቶች ይኖር የነበረውን ህዝብ በማገት፤ በማሰቃየት፤ ከመኖርያው በማባረር ንብረቱን በመዝረፍ ከቀዬው እንዲነቀል አድርጓል። በዚህም ህዝብ ተበታትኖ በጫካና ዋሻዎች እንዲጠለል አድርጓል። ከዓሊቴና ወንዝ ወደ ሰሜን ያለውን የኢሮብ መሬት ለሁለት ዓመት በሻዕቢያ ወራሪ ጦር ተይዞ የቆየ ሲሆን፤ ከእገታ ያመለጡ ዜጎች ወደ ዓዲግራት ከተማና ሌሎች የአከባቢ መንደሮች ነቅለው ለመውጣት ተገድዷል። ወራሪ ሠራዊቱም የተቆጣጠረውን የኢሮብ መሬት ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ሰው ወይም እንስሳ በረገጣቸው ቁጥር የሚፈነዱ ቦመቦችን በመሬት ውስጥ በመቅበር አከባቢውን ለወደፊት ህዝብ እንዳይኖርበት አድርጎታል። የሻዕቢያ ወራሪ ጦር በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ክፉኛ ተመቶ እንደተባረረም በተመድ ትብብር የተቀበሩ ቦምቦችን በባለሙያ ለማስለቀም የተደረገው ጥረት ከፍተኛ ጊዜና ገንዘብ ጠይቋል። ያም ሆኖ ግን ሻዕቢያ የቀበረው ቦምብ በሰውና በእንስሳት ላይ ያደርሰው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

ሻዕቢያ የኢሮብን መሬት እንደወረረ በአከባቢው የነበሩ ያሰተዳደርና የትምህርት ቤቶች ንብረቶች፤ እንዲሁም በገዳሞቻችንና በቤተክርስትያኖቻችን የነበሩትን የታሪክ መዛግብትና ንዋየ ቅዱሳንን በመዝረፍ የገዳማቱንና የቤተክርስትያናቱን አገልጋይ ካህናትና ደናግሎችን እንዲሁም ቀያቸውን ለቀው ለመሄድ ያልቻሉ ያገር ሽማግሌዎችንና አሮጊት እናቶቻችንን ሰብስቦ በማገት በእግራቸው ስንትና ስንት ኪ.ሜትሮችን በድካም፤ በራብና በውኃ ጥም እንዲሰቃዩና እንዲሞቱ አድርጓል። ከዚህም አልፎ፤ የዜግነታቸው መለያ የሆነውን ኢትዮጵያዊ መታወቂያቸውን ጥለው የሻዕቢያን መታወቂያ እንዲይዙ እስከማስገደድ ደርሶ ነበር። ይሁን እንጂ አንድም እንኳ የሻዕቢያን መታወቅያ ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ አልተገኘም። ኢሮቦች በኢትዮጵያዊ ማንነታቸው ላይ እንደማይደራደሩም በሞት አፋፍ ላይ ሆነውም አስመስክረዋል። ለኢትዮጵያዊ ማንነታቸውና ክብራቸው ዛሬም እንደወትሮው አልበገሬነታቸውን አስመስክሯል። ከዚህም ሌላ ሻዕቢያ አግቶ ከወሰዳቸውና እስከዚች ቀን ድረስ የደረሱበት የማይታወቅ፤ ከአንድ መቶ በላይ ኢሮብ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ለ16 ዓመታት ይኸው ደብዛቸው እንደጠፋ ቢሆንም ዜጎቼ ታግተው ተወስደውብኛል ብሎ የመጠየቅ ብቃት ያለው ኢትዮጵያዊ መንግሥት ማየት አልተቻለም። እነዚህ ታጋቾች መካከል ካህናትና ሌሎች የሃይማኖት መሪዎችም እንዳሉባቸው የምንዘነጋው አይሆንም።

ወደ ተሰዉት አርበኞቻችን ጉዳይ ስንመለስ፤ እነዚህ የኢሮብ አርበኞች እቅዱን ባያኮላሹበት ኖሮ የሻዓቢያ ምኞት ሰተት ብሎ የዓዲግራት ከተማንና አከባቢዋን መቆጣጠር እንደነበረ በኢሮብ ውስጥ ይዞታውን እያሰፋ ቁጥጥሩን ባጠናከረበት ወቅት ያደረጋቸው ሙከራዎች ምስክር ናቸው። የሻዓቢያ ሠራዊት የዳውሃን-ዓሊተናን ወንዝ ተሻግሮ በአዎ በኩል የነውንድፈን ሰንሰለትማ ተራሮችን በመዝለቅ ዓዲግራትን ከወደ ደቡብ ምሥራቅ ለማጥቃት ያልተሳካ እንቅስቃሴ አድርጎ ነበር። ሆኖም ቀድማ ለቅኝት የተንቀሳቀሰችው አሓዱ በህዝብ እይታ ውስጥ በመግባቷዋ የአካባቢው ምልሻና ህዝብ ሲያሳድዳት እግሬ አውጭኝ ብላ በመሸሽ ወደ ዓይጋ አከባቢ ብትመለስም፤ የሻዓቢያ ቃኝዎች በየጊዜው የዕንዱፈን ሰንሰለትማ ተራሮች ድረስ እየዘለቁ ህዝብን ያበሳብሱ ነበር። በዚህ የቃኝ እንቅስቃሴም ነበር ጠላት ማጋዑማ ድረስ በመዝለቅ በዓይጋው ጦርነት ከፈወተኛ ጀብድ ሠርተው በሕይወት በመትረፍ የጠላትን ጦር በድቢያ ውግያ ያንቀጠቀጡት ከላይ (በሁለተኛ የስም ዝርዝር ውስጥ) ከአንድ እስከ አራት ስማቸው የተጠቀሱትን አርበኞች ሕይወት ባረፉበት ቦታ ላይ የቀጠፈው። የኢሮብ ህዝብ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ነበር ሁለቱን ዓመታት በሻዕቢያ ወረራ ሥር ያሳለፈው።

ይህንን እብሪተኛ የሻዕያን ወረራ ለመመከት ሕይወታቸውን የሰጡ አርበኞቻችንን ማስታወስና ታሪካቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ የኛው በሕይወት ያለነው ዜጎች ግዴታ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። የአርበኞቻችንን መዘከር ግዴታችን ብቻ ሳይሆን ክብራችንም፤ ኩራታችንም ነው። "የፊተኛውን ወዳጅህን በምን ሸኘኸው? በሻሸ የኋላው እንዳይሸሸ" እንደሚባለው የዛሬ አርበኞቻችንን ካልዘከርናቸው ነገ አርበኞችን ማፍራት አስቸጋሪ ይሆናል። ስለሆነም፤ ግንቦት 23ን እንደ አርበኞች ቀን በመውሰድ ሰማዕታቶቻችን እንደሚከተለው አድርገን እንድንዘክራቸው ኢ.መ.ተ.ማ ጥሪውን ያቀርባል!

1. እነዚህን ለህዝብና ለአገር ክብር ሲሉ ውድ ሕይወታቸውን የሰጡ ሰማዕታት አርበኞቻችንን የቻልን በጋራ ተሰባስበን ያልቻልን ደግሞ በየቤታችን ሻማ በማብራት፤ ታሪካቸውን ለታዳጊ ልጆቻችን በማስተማር!
2. ዛሬ በኢሮብ ውስጥ እነዚህን አርበኞች የኢሮብ ህዝብ ተሰባስቦ በማስታወስ ታሪካቸውን ለወጣቶቹ ማስተላለፍ ተገቢ ቢሆንም ባለው ፖለቲካዊ ሁናቴ የማይቻል ስለሆነ ሀገርቤት ያለው ህዝባችን በያለበትና ሁኔታው በፈቀደው በሚመቸው መንገድ እንዲዘክራቸውና አጠቃላይ የሻዕቢያ ወረራና ያስከተለብን ማኅበራዊ፤ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ምን እንደሆነ ታሪኩ ተዘርዝሮ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ አስፈላጊው ዝግጅት እንዲደረግ!
3. የኢትዮጵያ ህዝብና የተለያዩ የፖለቲካም ሆነ የሲቪል፤ የሙያ፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ማህበራትና የተለያዩ የኢህአዴግ መንግሥት ጋር የመገናኘት መስመር ያላቸው ወገኖች ለ16 ዓመታት ሻዕቢያ አግቶ ያጠፋቸው ኢትዮጵያዊያን ዜጎቻችን ሁኔታን በሚመለከት በተመድ በኩል ይፋ ጥያቄ እንዲያቀርብ ግፊት እንዲያደርጉ መ.ኢ.ተ.ማ ጥሪውን ያቀርባል።
4. እንዲሁም ይህንን ሁላ ሕይወት የተከፈለበትና ህዝባችን ለሁለት ዓመት በሻዓብያ ወረራ ሥር የሰቆቃ ኑሮ የገፉበትን ሉዓላዊ የኢትዮጵያን ግዛት ለሻዕቢያ እንዳይሰጥ፤ የኢትዮጵያ ህዝብና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የበኩላቸውን ግፊት እንዲያደርጉ መ.ኢ.ተ.ማ ጥሪውን ያቀርባል።

ዘለዓለማዊ ክብር ለግንቦት 23 1990 ዓ.ም ሰማዕታቶቻችን!
በሻዓቢያ የታገቱ ወገኖቻችን ሕይወትን ለመታደግ ሁላችን የዓቅማችንን እናድርግ!

መ.ኢ.ተ.ማ ግንቦት 2006 ዓ.ም